የዲሴምበር 17 2017 የሕዝባዊ ሥብሰባ ዘገባ
ዋሺንግተን ዲሲ



ባለፈው ዕሁድ ዲሴምበር 17 2017 በዚህ በዋሺንግተን ዲሲ መዲና በድምቀት ተከናወነ። በሰማያዊ ፓርቲ፤ መኢአድና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ የተጠራ ሕዛባዊ ሥብሰባ በተሰካ ሁኔታ መጠናቀቅ ቀላቀባያችን በቦታው ተገኝቶ ዘግቦልናል። ይህን ታሪካዊ ጉባዔ ልዩ የሚያደርገውም ከላይ የተዘረዘሩት ሦስት ድርጅቶች ለረጅም ጊዜ ተካታታይ ውይይቶችን ካደረጉ በሁዋላ በጋራ ለመስራት መስማማታቸውን ይፋ ማድረጋቸው ሲሆን የድርጅቶዩ መሪዎች ፊርማቸውን ያሰፈሩበት ልዩ መግለጫ በእለቱ ለሕዝብ ተሰራጭቷል።

በጉባዔው ላይ በዶ/ር አክሎክ ቢራራ መክፈቻ እና ደ/ር ፍቅሬ ቶለሳ (በስካይፐ) በማከታተል ባቀረቡት ንግግር የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ የተንተራሰ ሰፊ ገለጻ ያደረጉ ሲሆን ዶ/ር አክሎክ ባገራችን ተደቅኖ ያለውን አደገኛ ጎሳ ተከል ችግር ለመታደግ ዋነኛ መፍትሄው በኢትዮጵያ ላይ ያተኮረ ብሔራዊ መግባት የመፍጠርን አስፈላጊነት አሳስበዋል። ዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ በማስከተል ባቀረቡት ንግግር ብዙ ክፍለ አገሮች ባላት ኢትዮጵያ የሕዝቦችዋ ባህል፣ ቋንቋና እምነት የሚከበርበት ሥርዓተ መዋቅርን መዘርጋት አስፈላጊነት አስምረወብታል።



የሰማያዊ ፓርቲ ልቀመንበር አቶ የሽዋስ አሰፋ፤ የመኢአድ ፕሬዝዳንት ዶ/ር በዛብህ ደምሴና የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ልቀመንበር ዶ/ር ታዬ ዘገየ በማከታተል ለውይይት ጠቃሚ የሆነ መነደርደሪያ አቅርበዋል።



የመኢአድ ፕሬዝዳንት ደ/ር በዛብህ ደምሴ “አማራጭ የፖለቲካ ድርጅት በኢትዮጵያ እንዴት” በሚል ርዕስ በቀረቡት ንግግር በኢትዮጵያ የተካሄዱ ትግሎች ተመክሮ በምሳሌነት በማጣቀስ፣ የሰማያዊ ትግልን አሸናፊነትና ትግሉንም ባንድነት አቀናጅቶ የማካሄድን አስፍላጊነት አብክረው አስገንዝበዋል።



የሰማያዊው ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ የሽዋስ አሰፋም “ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አስፈላጊ ነው” በሚል ርዕስ ያቀረቡትን ሲያብራሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አስፈላጊንት የማያጠያይቅ መሆኑን አስረግጠው፤ ነገር ግን እንዴት በሚለው አብይ ጉዳይ አተኩረው በሃያ-አንደኛው ክፍለ ዘመን የቅራኔ መፍች ዘዴ ሥልጣንን በዱላ መቀባበል መሆን የለበትም ሲሉ በማስገንዘብ በአገር ውስጥ የምንታገል ፓርቲዎች የሥርዓትን ለውጥ ለማምጣት የምንጠቀምበት መንገድ ጠብመንጃ መሆን

የለበትም ሲሉ በማስረገጥ ለለውጥ የሚደረገው ትግል ከክላሽ ወደ ካርድ መቀየር አለበት ሲሉ አጽንዖት ሰጥተዋል።



በመጨረሻ ተናጋሪ የነበሩት የኢትዮጵያ ሕዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ ልቀመንበር ዶ/ር ታዬ ዘገየ “የፓርቲዎች ሕብረትና ያኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል” በሚል ርዕስ ዙሪያ ባደረጉት ንግግር፤ አገሪቱ ውስጥ በተጨባጭ የታየው ወቅታዊ ሁኔታ፤ የገዢው እንደወትሮው እየረገጠ መግዛት ያልቻለበት በሌላ በኩል ደግሞ ሕዝብ አሻፈረኝ አልገዛም ያለበት ሁኔታ ላይ የደረስን መሆኑን ያመላከቱ ሲሆን በሦስቱ ፓርቲዎች መካከል የተካሔደውን የስምምነት ሰነድ ይፋ በማድረግ ሦስቱም ተናጋሪዎቹ የውይይት መንደርደሪያ ንግግራቸውን አጠናቋል።

የእለቱን የስብሰባ መርሀግብር በመምራት የተባበረው ታጋይ አክቲቪሰትና ጋዜጠኛ አቶ አበበ በለው ነበር። የፓርቲዎቹ ወኪሎች ከስብሰባ ታዳሚዎች ጋር ጠቃሚ ውይይትት አካሂደዋል።





በዝግጅቱ መሀልም በፕሮፌሰር አቻሜለህ ደበላ የተበረከተ ሥእል ለጨረታ ቀርቦ የተሰበሰበው ተዋጽኦ ወደ አገራቸው የስራ ጉብኝታቸውን አጠናቀው ለሚመለሱት የመአድና የሰማያዊ ፓርቲ በአገር ቤት ለሚካሄዱት ትግል እንዲውል ተበርክቶ ስብሰባው በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

በሥፍራው ከተገኙ የዜናና የመረጃ ተቋሞችም ውስጥ የ አሜሪካ ድምጽ (ቪ.ኦ.ኤ)፣ አባይ ሚድያ፣ አዲስ ድምጽ፣ ኢትዮፓናሮማ እና ራድዮ-ድሞክራሲያ ይገኙበታል።

ኢትዮፓኖራማ
ዲስምበር 2017